**የታካሚ መብት እና ግዴታ**

የታካሚን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ከጤና እንክብካቤ ሰጪ ቡድንዎት ጋር በግልጽ እንዲነጋገሩ፣ ስለሁኔታዎች በደንብ እንዲያውቁ እና በእንክብካቤ ውሳኔዎች እና የህክምና ምርጫዎች ላይ እንዲሳተፉ እናበረታታለን። ለታካሚዎች እና የታካሚዎች ተወካዮች ከስር የተዘረዘረውን መብት እና ግዴታ በመገምገም የጤና እንክብካቤ ሰጪ ቡድንዎት ንቁ አባል ነው እኛን ይቀላቀሉ።

## እርስዎ እና የመረጡት ሰው የሚከተሉት መብቶች አሉት፡

### አክብሮት የተሞላው እና ተገቢ እንክብካቤ መስጠት

1. ነገሮችን ያገናዘበ፣ አክብሮት እና ርህራሄ የተሞላው እንክብካቤ መስጠት።
2. ስፒታል ወይም ድንገተኛ ክፍል ሲገቡ፣ ሲዛወሩ ወይም ሲወጡ ለቤተሰብዎ አባል/ጓደኛዎ እና   ክተርዎ ያሳውቁ።
3. ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ፣ ችላ ከመባል እና ከጥቃት (የቃል፣ አዕምሮ፣ አካል ወይም ወሲባዊ ጥቃት) ነጻ የነ እንክብካቤ መሰጠት።
4. ለአደጋ ጊዜ የህክምና ሁኔታ እና ምጥ የህክምና ምርመራ መደረግ እና የሚያረጋጋ ህክምና መሰጠት።
5. ለደህንነት አስፈላጊ ካልነ በስተቀር ከመያዝ/መታሰር እና ተነጥሎ ከመቀመጥ ነጻ መን።
6. እንክብካቤ የሚሰጥዎትን ሰው ስም እና ስራ ማወቅ።
7. በእንክብካቤ አሰጣጥ ውስጥ ተማሪዎች፣ ሬዚደንትስ ወይም ሌላ ሰልጣኝ ሲሳተፍ ማወቅ።
8. የባህልዎት እና የግል መርዎች፣ እምነቶች እና ፍላጎቶች መከበር።
9. የመንፈሳዊ አገልግሎቶች ማግኘት።
10. ከእንክብካቤዎት ጋር በተያያዘ ከስነ-ምግባር አገልገሎት ጋር መነጋገር።
11. በዘር፣ ቀለም፣ ሀገር፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ ጾታዊ መለያ ወይም መገለጫ፣ አካላዊ ወይም አዕምሯ ጉዳት፣ ሀይማኖት፣ ብሄር፣ ቋንቋ ወይም የመክፈል ችሎታ መሰረት ያለመድልኦ መታከም።
12. አስፈላጊ ሲን የጥበቃ እና የማበረታታት አገልግሎት መሰጠት። እነዚህ አገልገሎቶች የተወሰኑ ታካሚዎች (ለምሳሌ ልጆች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች) መብታቸውን እንዲጠቀሙበት እና ችላ ከመባል እና ከጥቃት ለመጠበቅ ይረዳሉ።
13. የስፒታሉንና የሃኪሞን ክፍያን መረጃ መውሰድ።
14. እንክብካቤው ከመሰጠቱ በፊት ግምታዊ የስፒታል ክፍያን መጠየቅ።

### እንክብካቤ ሲሰጥ ውጤታማ መግባባት እና ተሳትፎ

15. እርስዎ በመረጡት እና በግል   በሚረዱት መንገድ (ለምሳሌ   የምልክት ቋንቋ፣ የእይታ እገዛ፣ የቋንቋ ትርጉም) መረጃ ያግ እነዚህ አገልግሎቶች በነጻ ይሰጣሉ።
16. ስለሚከተሉት ከሀኪምዎት/አገልግሎት ሰጪዎት መረጃ ማግኘት፡
    - ምርመራዎት
    - የምርመራ ውጤቶችዎት
    - የተጠበቀ የእንክብካቤው ውጤትና ያልተጠበቀ የእንክብካቤው ውጤት
17. በእንክብካቤዎት እቅድ እና የእቅዱ መተግበር ላይ መሳተፍ ወይም በማንኛውም ሰዓት የእቅዱን ትግበራ ግምገማ መጠየቅ።
18. ስለእንክብካቤው የሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ ቤተሰብዎትን ማሳተፍ።
19. ጥያቄ መጠየቅ እና ለጥያቄዎችዎ  በወቅቱ ምላሽ ማግኘት።
20. ስቃይዎት እንዲቀንስ መደረግ።
21. እንክብካቤ አለመቀበል።
22. ለስሜታዊ እገዛ ሰው አብሮዎት እንዲን ማድረግ፤ ያሰው ከእርስዎ እና ከሌሎች መብት፣ ደህንነት ወይም ጤና ጋር የማይቃረን ከነ።
23. በ  ኪም ምርመራዎች፣ በላ  ራቶሪ ምርመራዎች ወይም በህክምና ሂደቶች ወቅት አብረዎት የሚ  ንን ሰው ይጠይቁ እና ያግ  ።
24. የሚያግዝዎትን ሰው እና የሚጎበኙዎትን ሰው መምረጥ እንዲሁም የሚጎበኙዎት ሰው መቀየር።
25. የጤና እንክብካቤን በተመለከተ ውሳኔ መወሰን የማይችሉበት ጊዜ ካለ በዚህ ጊዜ የሚወስንልዎት ሰው መምረጥ (እንዲሁም ሁሉም የታካሚ መብቶች በዛ ሰው ላይ እንዲተገበሩ ማድረግ)።

JOHNS HOPKINS
JOHNS HOPKINS HEALTH SYSTEM

### ህይወትን የማሳለፍ ውሳኔዎች

26. አስቀድመው መመሪያ (ሌላ ስሙ የጤና እንክብካቤ የቁም ኑዛዜ ወይም ዘላቂ ውክልና ይባላል) ማዘጋጀት ወይም መለወጥ፡፡
27. ከተቻለ የአካል መስጠት ፍላጎትዎ እንዲታወቅ እና እንዲከበር ማድረግ፡፡

### እውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ

28. ከአደጋ ጊዜ ውጪ የነ እንክብካቤ ከመሰጠቱ በፊት ፈቃድ (እውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ) መስጠት፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፡
    - የህክምናዎት አደጋ እና ጥቅም
    - የህክምናው ሌላ አማራጭ
    - የሌላኛው አማራጭ አደጋ እና ጥቅም
29. እንክብካቤዎት ላይ አስተዋጽኦ ሳያደርግ የምርምር ጥናት አካል ለመን መስማማት ወይም አለመስማማት፡፡
30. ከግል እንክብካቤዎ ውጪ ለ  ኑ ማንኛውም ምክንያት የምስል፣   ዲዮ ወይም የድምጽ ቅጂዎችን ለመፍቀድ ይስማሙ ወይም እምቢ ይበሉ፡፡

### ግላዊነት እና ሚስጥራዊነት

31. ግላዊ እና ሚስጥራዊ ህክምና እና መግባባት/መነጋገር ማድረግ፡፡
32. የግላዊ ተግባር HIPAA ማስታወቂያ ቅጂ መቀበል የህክምና መረጃዎትን ያካትታል

## የሚከተሉት ሀላፊነት አለብዎት፡

1. ስለጤናዎት፣ አድራሻዎት፣ ስልክ ቁጥር፣ የልደት ቀን፣ ኢንሹራንስ ያዥ እና ቀጣሪ ትክክለኛ እና ሙሉ መረጃ መስጠት፡፡
2. በቀጠሮ መገኘት ካልቻሉ መደወል፡፡
3. የስፒታሉን    ሰራተኞች ማክበር፤ ከሀኪሙ ጀምሮ እስከ ነርስ፣ ቴክኒሺያን፣ ምግብ አቅራቢ እና ጽዳት ድረስ ማክበር አለብዎት፡፡
4. ቋንቋን እና የሌሎች ሰዎችን ተግባር እና ንብረት ከግንዛቤ ማስገባት ለምሳሌ የድምጽ ከፍታን፣ ግላዊነትን እና የጠያቂ ቁጥርን ማገናዘብ ማለት ነው፡፡
5. ከተናደዱ እራስዎትን መቆጣጠር፡፡
6. የወደፊት መመሪያዎትን ቅጂ ለእኛ መስጠት፡፡
7. ያልገባዎት ነገር ካለ መጠየቅ፡፡
8. ጤናዎት ላይ ያልተጠበቀ ለውጥ ካለ ማሳወቅ፡፡
9. የስፒታል    ደንብ መከተል፡፡
10. እንክብካቤ እንዳይሰጥዎት በመከልከልዎት ወይም መመሪያዎች ባለመከተልዎት ለሚከተሉ ችግሮች ሀላፊነት መውሰድ፡፡
11. ውድ እቃዎችን ቤት መተው፡፡
12. ስለስፒታል    ሰራተኛ ወይም ሌላ ታካሚ ያለ መረጃ ሁሉ ለግል መያዝ፡፡
13. ከስፒታሉ    ሰራተኛ ፈቃድ ሳያገኙ ፎቶ አለማንሳት፣ ቪድዮ ወይም ድምጽ አለመቅረጽ፡፡
14. ያለብዎትን ሂሳብ መክፈል ወይም የሂሳብ ግዴታዎችዎትን ለመወጣት እርዳታ ለማግኘት ከእኛ ጋር መስራት፡፡

JOHNS HOPKINS

JOHNS HOPKINS HEALTH SYSTEM